በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

## የተሰጠ መግለጫ

ያካቲት 4ቀን 2006 ዓ.ም

# በፍርሃት እየኖሩ መብትና ነፃነት ማስከበር አይቻልም።

## መምህሩ በነፃ ሕሊና ትምህርቱን ካላስተላለፈ ነፃ አእምሮ ያለውን ትውልድ መፍጠር አይታሰብም።

አንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ) ከውልደቱ ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ ለቆመለት ዓላማ ማለትም ለመምህራን መብት መጠበቅ፣ ለአካዳሚክ ነፃነት መስፈን፣ ለመደራጀት መብትና ለትምህርት ጥራት ታግሏል።ለምሳሌ በ1959 ዓ.ም የትምህርት ሚኒስቴር የመምህራንን ደመወዝ እስኬል ያወጣወን በመቃወም በ1960ዓ.ም የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር የመምህራን ደመወዝ እንዲሻሻል ጥያቄ በማንሳት የሥራ ማቆም አድማ ማድረጉ ይታወሳል። በዚህም ድርጊቱ ማህበሩ ሙያው ከበሬታ እንዲያገኝ አስችሏል። በመቀጠልም በ1965ዓ.ም ዝግጅ ተጠናቆ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ለመዋል በዓለም ገንዘብ አበዳሪ ድርጅት (IMF) እና በዓለም ባንክ ( The World Bank) አማካይነት የተቀረጸውን የትምህርት ዘርፍ ከለሳ (Education Sector Review =ESR) ሴክተር ሪቪው በመባል የሚታወቀውን የድሃ ልጆች እንዳይማሩ የሚያደርገውን የትምህርት ፖሊሲ በመቃወም ለመምህራን የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ፣ ትምህርት ለሁሉም እንዲደረስ ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥሮዓት በአገሪቱ እንዲሰፍን ያካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም አገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ ሥርዓቱን እንዳናጋው ምንም ጊዜም ታሪክ የሚያነሳው አኩሪ ተግባር ነው። ከደርግ ውድቀት በኋላም አንጋፋው ኢመማ ከመመህራን የቀረቡ 20 ጥዎች አካቶ ነሐሴ ወር 1984ዓ.ም በወቅቱ ለነበረው የሽግግር መንግሥት ማቅረቡ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።ኢመማ ለአባላቱ መብት መጠበቅ፣ለአካዳሚክ ነፃነት እውን መሆን፣ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም በእኩልነት እንዲደረስ ለዚህም መሟላት እንዲያስችል ሕዝብ የተሳተፈበት የትምህርት ፖሊሲ እንዲቀረጽና ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲሰፍን አምርሮ ታግሏል።በዚህም ምክንያት አባላቱ በአጠቃላይ የአመራር አካላቱ በተለይ ለሞት ፣ ለእስር ፣ ለሰደትና ለተለያዩ ስቃዮች ተጋልጠዋል።

ረጅምና ጠመዝማዛ የትግል መስዋእትነት ተከፍሎበት እንደሰንደቅ ከፍ ብሎ ይታይ የነበረውን አንጋፋውን የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ያለህጋዊ መሰረት በመውረስ ሲንቀሳቀስ የቆየው በመንግሥት የሚደገፈው ኢመማ ተብዬ ተለጣፊ ማህበር በታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም በተወሰኑ ክልሎች በሚገኙ የዞን መስተዳድር ርዕሰ ከተሞች ከየት/ቤቱ በኮታ የተመረጡ መምህራንን በመሰብሰብ መንግሥት የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት የሚገኝበትን ቦታ ለኢንቨስተር(ለብሔራዊ ባንክ) ሊሰጠው ስለሆነ እኛ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ ጽ/ቤት በመገኘት ሁኔታውን አስረድተን ጠቅላይ ሚኒስትሩም እናንተ ህንፃ የምትሰሩበት አቅም ያላችሁ ከሆነ ቦታው ለኢንቨስተሮች እንዳይሰጥ ትእዛዝ አስተላልፋለሁ በማለት ቃል ገብተውልናል።እኛም በተገባልን ቃል መሰረት ቦታው ለሌላ ኢንቨስተር ተላልፎ እንዳይሰጥብን ባለ 36 ፎቅ ህንፃ ለማስገንባት እቅድ የያዝን ስለሆነ ለዚህ ህንፃ ግንባታ የሚሆን የማህበሩ አባል የሆናችሁ መምህራን በአንድ ዓመት ተከፍሎ የሚያልቅ የአንድ ወር ደመወዛችሁን እንድትሰጡን በማለት ጥያቄ አቅርበው ነበረ። ይሁን እንጂ መምህራኑ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ እናንተ የኢመማን አላማ ፣ ደንብና ጥቅል የጉዞ ታሪኩን በመጣስ ከመምህሩ ጉያ የወጣችሁ ከሃዲዎች ለመምህርነት ሙያ ክብር ፣ ለትምህርት ጥራትና ለህዝባዊ ትምህርት በዕኩልነት በነፃ መዳረስ፣ ለዲሞክራሲና ፍትሐዊ ስርዓት መረጋገጥ በጽናት ቆመው የተሰዉና አሁንም መስዕዋትነት እየከፈሉ ካሉ የሙያው ተቆርቋሪ ከሆኑ ሀቀኛ መምህራን አንፃር ስንመዝናችሁ ታሪክን ያጎደፋችሁ፣ መምህሩን ያዋረዳችሁ፣ የጥፋት መልክተኞችና የገዥው ፓርቲ ተላላኪዎች እንጂ የመምህሩ ተወካይ አይደላችሁም ። ተወካዮች ነን የምትሉ ከሆነ የመወያያ አጀንዳ ብላችሁ ባቀረባችሁት ሳይሆን መወያየት ካለብንም መወያየት የምንፈልገው እኛ የምንላችሁን የከፋና ስር የሰደደ የትምህርትና የመምህራንን ችግር አዳምጣችሁ ማስታወሻ ይዛችሁ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለትምህርት ሚኒስትሩ ታደርሱ ከሆነ እንወያይ ይህ ካልሆነ ውይይት አያስፈልግም



P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*በማለት ታዳሚው በአንድ ድምጽ አስተጋባ። በዚህም መሰረት ሰብሳቢዎቹ ያለውዴታቸው በግዴታ ታዳሚዎቹ ባቀረቡት ሀሳብ መሰረት ስብሰባው ቀጥሎ የሚከተሉት አንኳር አንኳር ጥያቄዎች ቀረቡ።*

- *የእናንተ ኢመማ ወገንተኝነቱ ለማን ነው?*
- *የመምህርነት ሙያ ተገቢውን ክብር ሲነፈግ ምን እየሰራ ነበር?*
- *የመምህራን የሥራ ነፃነትና ዋስትና በሌለበት እንዴት የትምህርት ጥራት ሊመጣ ይችላል?*
- *ከትምህርት ሽፋን ይልቅ ለጥራቱ ትኩረት የማይሰጠው ለምንድነው? የትምህርት ጥራት መንግስት እንደሚያወራውና እየሰራሁ ነው ከሚለው እጅግ በተለየ መልኩ ከመቼውም ጊዜ በላይ ወድቋል፤ሞቷል። በዚህ ረገድ የእናንተ ኢመማ ምን እየሰራ ነው?*
- *የትምህርት ጥራት ከመምህራን ጥቅማጥቅምና የሥራ ነዋስትና ጋር በእጅጉ ይያያዛል።በአሁኑ ጊዜ መምህሩ ከእጅ ወደ አፍ እንኳን ባልሆን የኑሮ ውድነት እየተንገላታና እየዳሸቀ ይገኛል። የመምህራንን ኑሮ ለማሻሻልና የሥራ ዋስትናቸውን ለማጎናፀፍ የደረጃ እድገትና መንግሥት በ2004 ዓ.ም ፈቅጃለሁ ብሎት የነበረውን የጎንዮሽ የእርከን ጭማሪ የውሃ ሽታ ሆኖ ሲቀር መንግሥት ተግባራዊ እንዲያደርግ ኢመማ ተብዬው ከመንግስት ተለጣፊነት ወጥቶ ከሆነ ምን እየሰራ ነው?*
- *የቀድሞው መምህራን ማህበር ለማሰራት አስቦት የነበረው የመምህራን ሆስፒታል ግንባታ ከምን ደረሰ?*
- *ከቀድሞው መምህራን ማህበር በመንግሥት እየታገዛችሁ "በሕግ ሽፋን " የወረሳችሁትን ከአስር ሚሊዮን ብር በላይ የት አደረሳችሁት?*
- *በሃገሪቱ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል የማይደረገው ለምንድነው?*
- *መምህራን ለተለያዩ የስራ መደቦችና ሥልጣናዎች ሲወዳደሩ መሰፈርት ሁነው የሚሰራባቸው መመዘኛዎች ከፖለቲካ ይልቅ ሥራ ተኮርና ልምድን መሰረት የማያደርጉት ለምንድን ነው?*
- *በአዲስ መልክ ታተመ የተባለው የመማሪያና ማስተማሪያ መጸሐፍት ከአላማቸው የወጡ ይዘታቸው እጅግ የተንዛዘ ከዚህም ከዚያም የተግበሰበሱና የአገሪቱን ነበራዊ ሁኔታዎችን ያላገነዘቡ መሰረታዊ ጭብጥ በሌላቸው መረጃዎች የታጨቁና በባለሙያዎች ሳይሆን በሥርዓቱ ካድሬዎች የኢድርጉ ትእዛዝ የተጻፉና የታተሙ፣ ለእርዳታ መጠየቂያና ማግኛ ሲባል በይድረስ ይድረስ የተዘጋጁ የትምህርት ጥራት እንዲሞት ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ናቸው።ይህ ሁሉ ሲሆን የእናንተ ኢመማ ድርሻ ምን ነበር?*
- *ዩኒቨርስቲዎች ምንም እውቀትና ችሎታ በሌላቸው ከተማሪዎቹ በማይሻሉ የኢህአደግ አባል በሆኑ ወጣት መምህራን የተሞሉ መሆናቸውንስ ታውቃላችሁ? ካወቃችሁስ በ2ኛ ደረጃ የሚገኙ አንጋፋና የጠለቀ እውቀት ያላቸው መምህራን በዩኒቨርስቲ መምህርነት እንዳይሳተፉ ለምን ተፈለገ?*
- *መምህራን ከታች እስከ ላይ ሙያቸውንና እውቀታቸውን መሰረት ያላደረጉ የቅጻቅጽ መሙላት ሥራ ተጠምደውና አንድ ለአምስት የቡድንና የልማት ሰራዊት ማደራጀት ሥራ ተውጥረው ሙሉ ቀን ትምህርት ቤት እንዲውሉ ሲደረግ ይህንን የማይቀበሉ ሲጎነተሉ ፤ሲሸማቀቁ ፣ ዛቻና ማስፈራራት ሲደርስባቸው ማህበር ተብዬው ምን እየሰራ ነው?*

*እውነተኛ ወኪሎቻችን ከሆናችሁ ይህንን ጥያቄአችንን በተገቢው መንገድ ለበላይ አካል አድርሱ ፤ ተከታትላችሁም አስፈጽሙ ፤ካልሆነላችሁ በታሪክ ተጠያቂ ላለመሆን ማህበሩን ልቀቁ የሚል ማሳሰቢያ ተሰጥቶ እነርሱም ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቶ የመጡበትንም የሕንፃ ግንባታ መዋጮ ሳያስፈጽሙ አፍረው፣ ተሸማቀውና ተዋርደውና አንገታቸውን ደፍተው ወደ መጡበት ለመመለስ ተገደዋል።*

*በእለቱ ሥርዓቱ ብቻውን አየር ላይ የተንጠለጠለ ግዑዝ አካል መሆኑን የሥርዓቱ ደጋፊ አባላት ሳይቀሩ በከፍተኛ ደረጃ ተቃውመው ሥርዓቱ ፀረ ልማትና ፀረ ትምህርት መሆኑን ከአንድ ጎሳ የተውጣጡ የማህበር ተወካይ ነን ባዮች ከመረረው የመምህራን የብሶት ድምጽ ተረድተው ተመልሰዋል።*

*ምንም እንኳን መምህራን የተለያዩ ፈታኝ ጥያቄዎችን በማንሳት ምሬታቸውንና ብሶታቸውን በአንድ ድምጽ ያስተጋቡ ቢሆንም መብታቸውን ለማስከበር የሚጠበቅባቸውን ያህል ተግባራዊ እንቅስቃሴ አላደረጉም።ለዚህም ማሳያ ሊሆን የሚችለው በ2004 ዓ.ም ለመምህራን የተደረገው የደሞዝ እስኬል ማሻሻያና በየዓመቱ ይሰጣል የተባለው የጎንዮሽ የእርከን*

*ጭማሪ ከወቅቱ የኑሮ ውድነት አኳያ በቂ አይደለም ብለው ያማረሩ የአንዳንድ ትምህርት ቤቶች መምህራን ጀምረውት የነበረው የስራ ማቆም አድማ እንቅስቃሴ በሌሎች ትምህርት ቤቶች መምህራን ባለመታገዙ ተኮላሽቶ የቀረበትን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል። ይህ የሚያመለክተው በሃገራችን በትምህርትና በመምህራን ላይ ሲፈፀሙ ከምናያቸው በደሎች አንፃር መምህራን ለመብት ማስከበር የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ ጎልቶ ያለመታየትና ሕብረትም አለመፍጠር ፣ ከሌሎች ከሚተጋሉ የማሕበረሰቡ አካላት ጋር አለመጣመር ዋናው መንስኤ በፍርሃት ቀንበር መውደቅ ነው። የእለት እንጀራዬን አጣለሁ፤ ቤተሰቤ ይራባል፤ ለባሰ መከራ እጋለጣለሁ ከሚል ስጋት በመነጨ መምህራን መብቶቻቸው ሲነኩ ሲሸራረፉና ሲጣሱ በራሳቸው ቸልተኝነት እንዲያልፏቸው ፍርሃት አስተዋጽኦ አድርጓል። የመምህራን ነፃነት ካልተከበረ ሕጋዊ መብታቸውና የትምህርት ጥራት ሊከበር አይችልም።**መምህሩ በነፃ ሕሊና ትምህርትን ካላስተላለፈ ነፃ ህሊና ያለውን ትውልድ መገንባቱ አይታሰብም።** የነፃነትን ዋጋ ያላገኘ ትውልድ የህሊና ብርታት አይኖረውም። መምህሩ እራሱን ከፍርሃት አላቆ ነፃነቱን ለማስከበር ፣ መብቶቹንና ጥቅማጥቅሞቹን ሳይጓደሉ የሚያገኝበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የራሱ የሆነ ነፃ ማህበር መመስረት ሲችል ብቻ ነው። ትምህርትና የማስተማር ሙያ ለራስና የራስ ልጆችን ለማሳደግና ደመወዝ ለማግኘት ሲባል ብቻ የሚከናወን ተግባር አይደለም።*

*መምህራን መብታቸውና ጥቅማጥቅማቸው ባለመከበራቸው የስራ ነፃነትና ዋስትና እያጡ በመምጣቱ ምክንያት የማስተማር ስራቸውን እየተው በከፍተኛ ደረጃ በመላ ሃገሪቱ በመፍለስ ላይ ይገኛሉ። ይህም ፍልሰት የትምህርትን ስራ ከመቼውም ጊዜ በላይ እያሽመደመደው ይገኛል። በተለይም በአዲስ አበባ ከፍተኛ የመምህራን ፍልሰት በመኖሩ ምክንያት የትምህርት ቢሮው በየጊዜው አዳዲስ መምህራንን ለመቅጠር የተገደደበት ሁኔታ ይስተዋላል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ በሽመልስ ሃብቴ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ብቻ ከ20 በላይ መምህራን በ2006 ዓ.ም በአንደኛው ሴሚስተር ስራቸውን ለቀው ሄደዋል። ከነዚህም ውስጥ ሁሉም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ( Information –Technology Department) መምህራን ስራቸውን ለቀው በመሄዳቸው ትምህርት ክፍሉ መዘጋቱና ተማሪዎቹም የመጀመሪያውን ሴሜስተር ፈተና ማን እንደሚፈትናቸው ምን እንደሚፈተኑ በውል የታወቀ ነገር የለም።*

*በሌላ በኩል በመምህራን ላይ እየደረሱ ካሉ ጫናዎች አንዱ ለአባይ ግድብ ግንባታ ለ2ኛ ጊዜ የወር ደመወዛቸውን በአንድ በአንድ አመት ከፍለው እንዲጨርሱ የቀረበላቸው ጥያቄ ሲሆን ይህም ጥያቄ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል። መምህራን ለዚህ ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እናንተ ለልማት መዋል የሚገባውን የሃገራችንን ሃብትና ንብረት ዘርፋችሁ የቅንጦት መኪና ገዝታችሁ፣ ህንፃ ገንብታችሁ ፣ ልጆቻችሁን በግል ትምህርት ቤትና ውጭ አገር እያስተማራችሁ ፣ በመንንደላቀቅ እየኖራችሁ እኛ የምንበላው አጥተን በኑሮ ውድነት እየተንገፈገፍንና እየተሰቃየን ገንዘብ አዋጡ ብላችሁ መጠየቃችሁ ግብዝነታችሁን ፤ ጨካኝነታችሁን፤ ህሊናቢስነታችሁን፤ ሆዳምነታችሁንና ስግብግብነታችሁን የሚያመላክት ነው ። ስለሆነም የዘረፋችሁትን የሕዝብ ሃብትና ንብረት መልሳችሁ ለግድቡ ግንባታ አውሉት እንጂ ደመወዛችንን ልትነኩ አይገባም ስትፈልጉ ከሰራ አባሩን በማለት ጠንካራ ተቃውሞ አሰምተዋል።*

*በተለይም በደቡብ ክልል በዲላና በይርጋጨፌ የሚገኙ መምህራን ለሁለተኛ ጊዜ ለአባይ ግድብ አዋጡ ተብለው ሳይጠየቁ ደመወዛቸው በመቆረጡ ሊቆረጥብን አይገባም መልሱልን ብለው ቢጠይቁም ሰሚ በማጣታቸው የስራ ማቆም አድማ አደርገው ለዲላ መምህራን ያለፍቃዳቸው የተቆረጠባቸው ገንዘብ ሲመለስላቸው ለይርጋጨፌ መምህራን ግን ሊመለስላቸው ባለመቻሉ ለሁለተኛ ጊዜ የስራ ማቆም አድማ በማድረጋቸው የአንደኛው ሴሚስተር ፈተና እንደተስተጓጎለ ከአካባቢው ከተገኘ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል።*

*ስለሆነም መምህሩ በፍርሃት አለም እየኖረ መብትና ጥቅሙ እንዲሁም ነፃነቱ ሊከበር እንደማይችል አውቆ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሚገኙ የዲላና የይርጋ ጨፌ መምህራንን ፈለግ በመከተል ፤ ተደራጅቶ በአንድነት በጽናት በመቆም አገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ በመጥራት መብቱንና ነፃነቱን ለማስከበር ትግሉን አጠናክሮ እንዲቀጥል በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪውን ያስተላልፋል።*

*ከፍርሃት አረንቋ በመውጣት ተደራጅተን በአንድነት እንነሳ!!!*
*ኢመማ በመምህራን ትግል እውን ይሆናል!!!*